# የክቡር አባ ኪዳነማርያም ገብራይ የሕይወት ታሪክ
## 1920- 2007 ዓ.ም.

**"ሩጫዬን እስከመጨረሻው ሮጫለሁ፣ሃይማኖቴን ጠብቄአለሁ፡፡ ከእንግዲህ ወዲህ የጽድቅ አክሊል ተዘጋጅቶ ይጠብቀኛል፡፡"** (2 ጢሞ፣4፡7)

ክቡር አባ ኪዳነማርያም ገብራይ የካቲት 17 ቀን 1920 ዓ.ም. ከአባታቸው ከቀኝአዝማች ገብራይ ካህሳይና ከእናታቸው ከወ/ሮ ለምለም ገብረማርያም በመነኩሰይቶ ተወለዱ፡፡

አባ ኪዳነማርያም ከአባታቸውና ከእናታቸው ከተወለዱት አምስት ወንዶችና ሁለት ሴት ልጆች የመጀመሪያ የበኩር ልጅ ሲሆኑ ከዚሁ ቤተሰብ 3 ካህናት ተገኝተዋል፡፡

ዕድሜያቸው ለትምህርት ሲደርስ በጎልዓ በላዛርስት ማህበር ስር ይተደደር በነበረው ትምህርት ቤት የአንደኛ ደረጃ ትምህርታቸውን ተከታትለዋል ክቡር አባ ኪዳነማርያም ከልጅነታቸው ጀምሮ በጸሎተኛ ቤተሰብ በማደጋቸው በመልካም ባህሪያቸው ካህን የመሆን ብርቱ ጉጉት አደረባቸውና ወደ ዘርዓ ክህነት ት/ቤት በመግባት በአዲስ አበባ ንዑስ ዘርዓ ክህነት የሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸውን ፈጽመዋል፡፡

በ1940 ዓ.ም.ይህንን የክህነት ጥሪ መንገድ በመምረጥ ወደ ሮም ቫቲካን ውስጥ በሚገኘው ኢትዮጵያ ኮሌጅ ተልከው በኡርባንያና ዩኒቨርስቲ በፍልስፍና በሥነ መለኮት ትምህርት ተከታትለው ድግሪያቸዋን ተቀብለዋል፡፡

በ1947 ዓ.ም. ወደ ሀገራቸው ከተመለሱ በኃላ በጊዜው የኤርትራ ሀገረስብከት ጳጳስ በነበሩት ከብፁዕ አቡነ ያዕቆብ ገብረየሱስ እጅ ምስጢረ ክህነት ተቀበሉ፡፡

በ1948 ዓ.ም ለተጨማሪ ትምህርት ወደ እንግሊዝ አገር ተልከው በኬምብርጅ ዩኒቨርስቲ በእንግሊዝኛ ቋንቋና የማስተማር የትምህርት ዘርፍ በሚገባ አጠናቀው ተመርቀዋል፡፡

በ1950ዓ.ም. ወደ ሀገራቸው ኢትዮጵያ በመመለስ በብፁዕ አቡነ ኃይለማርያም ያዕቆብ የአዲስ አበባ ሀገረስብከት ጳጳስ ትዕዛዝ በዓዲግራት ሀገረስብከት ተመድበው በተለያየ የሃላፊነት ደረጃ ለአስራ ሰባት ዓመታት አገልግለዋል፡፡ይኼውም በቆሞስነት፥ በትምህርት አስተዳደር፥ እና በቤተክርስቲያን የሃላፊነት ቦታዎች ላይ የበኩላቸውን ድርሻ ተወጥተዋል፡፡

ከ1965 -1970 ዓ.ም ወደ አዲስ አበባ ሀገረስብከት ተዘዋውረው በመናገሻ አውራጃ በወልመራ ወረዳ በነበረው የአዲስ አበባ ንዑስ ዘርዓ ክህነት ት/ቤት ተመድበው በአስተዳደሪነት አገልግለዋል፡፡

እግዚአብሔር ወደራሱ የጠራቸውን አባታችንን ክቡር አባ ኪዳነማርያምን በመንግስቱ ክብር ያኑርልን፡፡ የሚወዷትና የሚያከብሯት እመ አምላክ ፡ኪዳነምሕረት ነፍሳቸውን ትቀበልልን፡፡ ለሚወዷት ቤተክርስቲያንና ቤተሰባቸው፡ለወዳጆቻቸው ሁሉ እግዚአብሔር መጽናናትን ይስጠን፡፡

ቤተ ሊቀ ጳጳሳት ዘካቶሊካዊያን ዘኢትዮጵያ